# ጥሩ ቃሪያ ጥሬ

ሃዘንና ደስታን ፣ ሞገድ አመጣና
ሹክ አለኝ በጆሮ ፣ መለስ ሞተ አለና
ላልቅስ ወይ ልደሰት ፣ ገባሁኝ ፈተና
የትኛውን ልተው ፣ የቱን ልምረጥና ?

ሃዘን ፣ ግባ አይባል ፣ ግራ የተጋባ
ደስታ ተቀምጦ ፣ ሃዘን ፣ ቤት አይገባ
ምርጫዬን ተጠቀምኩ ፣ ፍርድ ሳላዛባ ።

ደስታን ሸኘሁት ፣ ይሂድ ምናባቱ
ሃዘንን ተቀበልኩ ፣ ይሰንብት ከቤቱ
ሰው እንዳያዝንብኝ ፣ ያልገባው ብልሃቱ ።

ግር አትሰኙብኝ ፣ በማንሸዋረሬ
ህሊናዬን ስቼ ፣ አይደለም ሰክሬ
ነገሬን ተረዱኝ ፣ ይግባችሁ ሚስጥሬ ።

የማልጠብቀውን ፣ ዛሬ በመስማቴ
መለስ ፣ ሞተ ቢሉኝ ፣ ፈሰሰ ሃሞቴ
ህልሜም አልሰመረ ፣ ተቆረጠ አንጀቴ ።

ለምን ሞተ ብዬ ፣ አላሰማ እሮሮ
ደስ ብሎኝ አልጨፍር ፣ አልመታ ከበሮ
ባገርና በህዝብ ፣ እንደቀለደበት
እንዴት ይሰናበት ፣ ይሂድ እንደዘበት ?

ሰማይ የነበረ ፣ ወድቆ ሲገፈተር
ሆድ በባሰው ዜጋ ፣ ታሽቶ ሳይወገር
ምኞቴ ሲከሽፍ ፣ ወጥቶ ሲቀር ካገር
ለምን አልከፋ ፣ በሰፈረው ቁና ፣ እሱም ሳይሰፈር ።

በሰፈረው ቁና ፣ ለሱም ተሰፍሮለት
ለእግሩ ካቴና ፣ እጅ ሙቅ ገብቶለት
ሲጎተት ሳላየው ፣ ታስሮ በሰንሰለት
ሲቀር ፣ ከፋኝ እንጂ ፣ የተመኘሁለት ።

ፈላጭና ቆራጭ ፣ አገር የበደለ
ሳይዘሩት የመጣ ፣ አረም የበቀለ
ህዝብን ያሰቃየ ፣ በግፍ የገደለ
ለምን ይሙት መለስ ፣ ብድር መች ከፈለ ።

ቁንጫና ትኋን ፣ አጅቦ መች ሸኘው
የስር ቤቱን ደጃፍ ፣ መች ገባ ፣ መች ቃኘው
መከራና ሃዘን ፣ ቤቱን አልጎበኘው
ምን አገኘሁ ብዬ ፣ እራሴን ላሞኘው
አጅሬ ደስታን ፣ ከወዴት ላግኘው
እርቋል ከኔስጋ ፣ አልመጣም ብመኘው ።

በደም የታጠበ ፣ አገር ያፈረሰ
ሞተ ብለው ቢሉኝ ፣ ሄደ ገሰገሰ
አለቀስኩ ለራሴ ፣ መቼ ለመለሰ
የልቤም አልሞላ ፣ አንጀቴም አልራሰ ።

የሙባረክ ውርደት ፣ ቡጢ ፣ እንደ ጋዳፊ
እርግጫ ሳይቀምስ ፣ ጥሩ ቃሪያ ጥፊ
ኮቸሮ ሳይበላ ፣ ሳይለብስ እራፊ
ሞተማ አትበሉኝ ፣ ሁሉም ነው አላፊ
አመለጠ በሉኝ ፣ ሄደ ያ ቀጣፊ ።

ታዛቢው . . . August 4,2012